በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 210711
ሕዳር 30 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ አዱኛ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አየሉ ታደሰ

2. ታሪኩ ታደሰ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 23/10/ 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 80590 በቀን 16/03/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 258188 ሚያዝያ 06 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የከተማን ይዞታ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ቁጥሩ 123(ሐ) የሆነው ቤት ባለይዞታ መሆናቸውን፤ 2ኛው ተጠሪ ይህንኑ ቤት አስመልክቶ በመ.ቁ 71430 አቅርበውት የነበረው ክስ ውድቅ ሆኖባቸው ሳለ በሌላ መዝገብ ባስወሰኑት ውሳኔ መነሻነት አፈጻጸም ከፍተው የሚመለከታቸውን አካለት በማሳሳት ቤቱን በአፈጻጸም የተረከቡት መሆኑን በመግለጽ ክስ የቀረበበትን ቤት መልሰው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲያስረክቡአቸው እና ለ10 ወራት ቤቱን አከራይተው ያገኙትን ብር 17,500 / አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ / እንዲከፍሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በሰጡት መልስ ክሱ በድጋሚ የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጡት መልስ ደግሞ አመልካች ከአውራሻችን አንድ ክፍል ቤት ተከራይተው ኪራይ ሲከፍሉ ቆይተው አውራሻችን በሞት ሲለዩ በወቅቱ የመብራት ለመክፈል ከአቅም በላይ ሆኖብን ሲቆረጥ በስማቸው መብራት አስገብተዋል፤ አከራካሪው ቤት የአባታችን የውርስ ሀብት ነው፤ አመልካች ቤቱ ይገባኛል ከማለት በቀር በምን አግባብ ቤቱን እንዳገኙት ለማሳየት ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ አመልካች በአፈጻጸም መዝገብ አቤቱታ አቅርበው ውደቅ ተደርጎባቸዋል፤ ተጠሪዎች ቤቱን የተረከብነው አስፈጻሚ አካላትን አታለን ሳይሆን በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም በመ.ቁ 123407 በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት ነው፤ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል በሰጠው ምላሽ በግቢው ውስጥ የመንግስት ቤት እንደሌለ እና በአገራባች ቁጥር ውስጥ አመልካች የጠቀሱት የቤት ቁጥር እንደሌለ ተረጋግጧል፤ ተጠሪዎች የአመልካችን ቤት አላከራየንም፤ ስለሆነም ክሱ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በብይን ውድቅ አድርጓል፤ በፍሬነገሩ ላይ ደግሞ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ እና የመ.ቁ 123407 የሆነው መዝገብ በትዕዛዝ አስቀርቦ ከተመለከተ በኂላ የቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 05 አስተዳደር ጽ/ቤት በቀን 06/02/2011 ዓ.ም ለቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ በተጠሪዎች አባት ይዞታ ውስጥ የምናስተዳድረው የቀበሌ ቤት ውስጥ የለም በማለት ገልጾአል፤ ተጠሪዎች በመ.ቁ 101280 በቀን 11/4/2009 ዓ.ም በተሰጠ ፍርድ በቦሌ ክፍለከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 123 የሆነው ቤት የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ስለሆነ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ተወስኗል፤ አመልካች የመ.ቁ 123407 በሆነው የአፈጻጸም መዝገብ አቤቱታ አቅርበው አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረቡ እና ፍርዱ ተፈጽሞ የተጠናቀቀ በመሆኑ በቤቱ ላይ መብት አለኝ የሚሉ ከሆነ ክስ አቅርበው ከሚጠይቁ በቀር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ተደርጎባቸዋል፤ በመ.ቁ 71430 ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በማስረጃ አልተደገፈም ተብሎ ውድቅ ከመደረጉ በቀር ለአመልካች መብት አልፈጠረም፤ ተጠቃሹ ቤት የመንግስት ቤት ካልሆነ አመልካች የግላቸው ስለመሆኑ ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፤ አመልካች ቤቱ የግላቸው ስለመሆኑ ያላስረዱ በመሆኑ ቤቱ ይመለስልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት የይግባኝ አቤቱታውን ሰርዞታል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በቀን 23/10/2013 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- 2ኛ ተጠሪ በመ.ቁ 71430 አስቀድመው አቅርበውት የነበረው ክስ ውድቅ ተደርጎባቸዋል፤ በመጀመሪያው ክስ በወረዳው ውስጥ ኗሪ መሆኔ እና ካርታ ለማውጣት በዝግጅት ላይ የነበርኩ መሆኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በተገለጸበት ሁኔታ ተጠሪዎች ለቤት ቁጥር 123 በከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ አሳስተው የተረከቡትን ቤት ለመረከብ ያቀረብኩትን ክስ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በመ.ቁ 71430 አመልካችን ተከሳሽ በማድረግ በመሰረተው ክስ አስተዳደሩ አመልካች በራሱ ይዞታ ውስጥ እንደሚገኝ ገልጾ 2ኛ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ተወስኖ ሳለ 2ኛ ተጠሪ ይህን ውሳኔ ሳያሽር በአፈጻጸም የቤቱ ባለመብት የሆነበት አግባብ ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪዎች ጥቅምት 22 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- 2ኛ ተጠሪ ቤቱን የተረከብኩት በመ.ቁ 84805 የ1ኛ ተጠሪ ወላጅ እናት የሆኑት የሟች ወ/ሮ አቻሜ ጨንገሬ የውርስ ሐብት ተጣርቶ ክርክር የተነሳበት ቤት እና ይዞታ የ2ኛ ተጠሪ ወላጅ አባት እና ባለቤታቸው የነበሩት ወ/ሮ አቻሜ ጨንገሬ መሆኑ ተረጋግጧል፤ በዚሁ መሠረት ክፍፍል እንዲደረግ በመ.ቁ 101280 ክስ ቀርቦ ተጠሪዎች ቤቱን እንድንካፈል ተወስኗል፤ ይህን ተከትሎም የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተሰጥቶ ቤቱ እኩል ታክፍሎ ተረክቤአለሁ፤ የቤት ቁጥር 123/ሐ በሚል የተደለደለ ቤት የለም፤ አመልካች ቤት ቁጥር 123/ሐ ማለት የጀመሩት ከጊዜ በኋላ ነው፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ ከሣሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222 መሠረት አዘጋጅቶ ከሚያቀረበው የክስ ማመልከቻ ጋር ለጉዳዩ ማስረጃ ይሆኑኛል የሚላቸውን የሠውም ሆነ የጽሁፍ ማስረጃዎችን ዝርዝርና ዋናውን ወይም ትክክለኛ ግልባጮቻቸውን ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 እና 234 ድንጋጌዎች ስር የተደነገገ ሲሆን የግራ ቀኙ ክርክር በቃል ተሰምቶና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 246፣ 247፣ 248 እና 249 ድንጋጌዎች አግባብ ተገቢው ጭብጥ ተይዞ ለጉዳዩ በሕጉ አግባብ የቀረቡት የተከራካሪ ወገኖች ማስረጃዎች ተሰምተውና አስፈላጊ ሲሆንም በሕጉ አግባብ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዲቀርቡ በማድረግ ጉዳዩ በሚገባ ተጣርቶ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 138፣ 257፣ 258 እና 259፤ 181 እና 182 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝቡናል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች የአከራካሪው ቤት ባለይዞታ ነኝ፤ ተጠሪዎች መብት እና ጥቅም ሳይኖራቸው ቤቱን ይዘውብኛል በማለት ከመከራከር በቀር በእርግጥም ይህን ክርክራቸውን የሚደግፍላቸውን ማስረጃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያቀረቡ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አያመለክትም፤ ይልቁንም ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ተጣርቶ እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ከቀረበው ምላሽ እና በተለያዩ መዝገቦች ከተሰጠው ውሳኔ ይዘት የተረጋገጠው ፍሬነገር አከራካሪ የሆነው ቤት በሚገኝበት ይዞታ ውስጥ ቀበሌው የሚያስተዳደረው ቤት የሌለ መሆኑን፤ ተጠሪዎች ቤቱን የተረከቡት የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ስለሆነ እኩል እንዲካፈሉ በማለት የተሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም በተከፈተ የአፈጻጸም መዝገብ በተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠረት መሆኑን፤ ተጠሪዎች አስቀድሞ በመ.ቁ 71430 አቅርበውት የነበረው ክስ በማስረጃ አልተደገፈም ተብሎ ውድቅ ከመደረጉ በቀር ለአመልካች የፈጠረው መብት የሌለ መሆኑን እና አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ የተረጋገጠ ፍሬረገር መሠረት በማድረግ አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን ስላላስረዱ ቤቱን ለመረከብ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሳኔ በሕግ አግባብ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 80590 በቀን 16/03/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 258188 ሚያዝያ 06 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. ነሐሴ 28 ቀን 2014 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

**ማ/እ** **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም